# በኢትዮጵያዊነታችን ፅኑ አቋም፣
# በአረንጓዴ - ቢጫ -ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን
# ፍቅርና በሕዝባችን ወሳኝ ትግል
# እናሸንፍለን !

ከአስተዋይ በቀለ

አዳሜ ! !

የምድረ- መንጋ ተቃዋሚ ተብዬዎች ጭንጫ አእምሮና እንጭጭ አመለካከት ከወያኔ ነፃ ያወጣኛል ብለህ አታስብ ።

ወያኔን ከስሩ መንግሎ ሊገረስስና ሥራዓቱን ቀልብሶ፣ ጠራርጎ ኢትዮጵያን ሊያጸዳት፣ ሊያድሳት፣ እድገቷንና ደህንነቷን ሊያረጋግጥላት የሚችል ኃይል ለኢትዮጵያ፣ ለኢትዮጵያዊነትና ለብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ የቆመው አገር ወዳድ ብቻ ነው ። ይህ ሕዝባዊ ኃይል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ።

ይህ ሕዝባዊ ኃይል በማይናወጥ አንድነትና በፅኑ ያገር ፍቅር የተመሰረተ፤ መላ ኢትዮጵያን ያዳረሰና ያቀፈ፣ ለውድ አገሩ፣ለዜግነቱ፣ ለታሪኩ ፣ ለብሔራዊ ክብሩ፣ ለኩራቱ፣ ጠንካራ ፍቅርና ፅኑ አቋም ያለው በመሆኑ፤ ኢትዮጵያን ነፃ አውጥቶ ብሔራዊ ጥቅሞቿን የሚያድስ፣ አሃዳዊ አንድነቷንና ሉዓላዊነቷን እስከ አሜጋ ድረስ አረጋግጦ የሚያዘልቅ ታማኝና አሸናፊ ኃይል ነው ።

ወገን !

ያልገባው ካለ ልብ ብሎ በውል ይግባው።

የፖለቲካው፣ የመንግሥትና የስልጣን ባለቤት አገር ወዳዱ ሕዝብ ነው። ወያኔ ወይንም ተቃዋሚነን ባዮች ወይም የዲያስፖራ ሽምድምድና አፈራሽ ስብስቦች፣ቡድኖች፣ ድርጅት ተብዬዎች ወይም አቅራሪዎች ወይም ምሁራን ወዘተ... አይደሉም። እነዚህማ ጀብሃን ፣ ሻቢያን፣ አረቦችን፣ ጠላት አገሮችን፣ የጀርመንና የኖርዲክ ፕሮቴስታንቶችን እየሰሙ አገራችንን በመበጥበጥ እዚህ የዛሬው ችግር ላይ በመጣል በውስጧ የሚኖረውን ሁሉ እያስለቀሱት ነው።ስለሆነም ሁሏም ከሕዝባችን ብሔርዊ ቁጣ ልታመልጥና ልትድን አትችልም።

ሃቁ ይኸ ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን ሕዝብዊ ኃይልን አኮስሶ በማየትና በመናቅ የወያኔን ቀጣይነትና የጋርዮሽ ሥልጣንን የሚያመቻች ብሔርዊ የእርቅ ጉባኤ እንዲጠራ ወያኔን በሽፋንና በምስጢር እየለመኑና እያባበሉ ይገኛሉ።

ይህ አቋም ወያኔ ተዘፍዝፎ እንዲኖርና ኢትዮጵያን የመሸጥና የማፍረስ ተግባሩን እንዲያጠናቅቅ የሚያደርግ አደገኛ አካሄድ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፅኑ ያወግዘዋል ።
ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ በጥሞና እንዲታወቅለት የሚፈልጋቸው ፅኑ አቋሞች አሉት።

አገር፣ ኢትዮጵያዊነትና ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማን በመስዋዕት ላይ መስዋዕትነትን ደርቦ ደራርቦ የሚጠብቀው ዘለዓለማዊ አቋሙ፣ ፍቅሩ፣ ብሔራዊ መለዮው፣ ክብሩ፣ ታሪኩና ኩራቱ ነው። በዚህ አቋሙ ላይ የሚደረግ ሴራንና ማናቸውንም ዓይነት አፍራሽ እንቅስቃሴዎች፣ ዝማሬዎች፣ ቀረርቶዎች ወዘተ... ሁሉ ይዋጋል ።

ሊገረስሰውና ነቃቅሎ ሊጠራርገው ኢላማ ካደረገው ወያኔ ጋር አይደራደርም። ሐሳቡም፣ ልቡም፣ አእምሮውም ፣ የሰራ አካላቱም ፀረ- ወያኔ ነው ።

ለሥልጣን ከሚቋምጡ፣ የወያኔን በደል ለመክደንና አብሮ ለመስራት ከሚያሰፈስፉ ምድረ-መንጋ ተቃዋሚ ተብዬዎች ፣ ከአገር ጥቅሞች አንጻር ተቀባይነት ከሌላቸው ምሁራን፣ ለኢትዮጵያ መፍረስ ሰውር ጉድጓድ ከሚቆፍሩ፣ ከፖለቲካ መሸተኞች፣ ከባንዳዎች፣ ካድርባዮች ፀሐይ በቀትር እንዲትገባ፣ ጨረቃና ከዋክብት እንዲጋቡ እናደርጋለን ከሚሉ ቧግዲ አፈኞች፣ ሚዛናቸው ወደ ወያኔ ካጋደለና ካደላ ጋር ሁሉ ወዘተ... ሕዝባችን ያለው አቋም ተፃራሪና ፈጽሞ የማይታረቅ የከረረ ጠላትነት ነው።

አገር ወዳድ ነን እያሉ በአፋቸው የሚሸነግሉና ነገር ግን የአዲስ ድርጅትን ግንባታና ሥምሪት፣ ሃሳብና ጥሪ የሚያኮላሹና ወደኃላ የሚያፈገፍጉ ሁሉ ኪሳቸው ቢዳበስና ውስጣቸው ቢመረመር የሚጎለጎለው ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ሕዝብ ጉድ ብዙ እንደሆነ ሕዝባዊ ኃይል በጥሞና ይገነዘበዋል።

ወገን !
ሕዝብ በቅርቡ ከዳር እስከዳር ይነሳል። በኢትዮጵያዊነቱ ፅኑ አቋም፣ በብሔራዊ ስንደቅ ዓላም ፍቅር፣ በጋለ ወኔው፣ በቆራጥ ትግሉ አሸንፎ የአገርን ሕልውናና የበላይነቱን ያረጋግጣል ።

ወያኔ፣ ምድረ-መንጋ ተቃዋሚ ተብዮዎችና ሌሎች ፀረ- ኢትዮጵያ ሁሉ እየተለቃቀሙ በመደምሰስ የውሾችና የሰማይ ወፎች ሲሳይ ይሆናሉ።

አንተ ! ግን አገርህን የምትወድ ሕዝባዊ ከሆንክ ዛሬውን ሕዝብህን ደግፈህ ታገል።

*መሪና መንግሥት*

ከሕዝብ መካከል በሕዝብ ይወጣል ! !